# ማስታወቂያ

# ለዳሸን ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ በአስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት እንዲከናወን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የባንካችን የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ በባንኩ የባለአክሲዮኖች 22ኛ መደበኛ እና 20ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ መመረጡ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላትን ጥቆማ ከሚያዝያ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ብቻ የሚቀበል ስለሆነ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SBB/54/2012 እና SBB/62/2015 ላይ የተዘረዘሩ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩ የቦርድ አባላትን እንድትጠቁሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

1. የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ፣
2. ዕድሜው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣
3. በማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ፣
4. ሀቀኛ፣ ታማኝ እና መልካም ዝና ያለው፤
5. በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሠጥቶበት የማያውቅ፤
6. በሌላ የፋይናንስ ድርጅት የቦርድ አባል ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያልሆነ፣
7. በንግድ ሥራና በንግድ ሥራ አስተዳደር በተለይም በፋይናንስ ወይም በባንክ ሥራ የሥራ ልምድ ያለው ቢሆን ይመረጣል፤
8. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት፤
9. በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ ለዕዳ ማቻቻያ ያልተወሰደበት፤
10. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሃራጅ ያልተሸጠ፣ ተከሶ ያልተፈረደበት ወይም እሱ የሚመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረበት/ያልገባበት፤
11. በቂ ስንቅ/ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ሰጥቶ ሂሳቡ ያልተዘጋበት፤
12. ታክስ ባለመክፈል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ፤

13. የትምህርት ደረጃን በሚመለከት ከሚመረጡት የቦርድ አባላት መካከል ሰባ አምስት በመቶ (75%) የመጀመሪያ ድግሪ ወይም ከዚያ በላይ እንዲሁም ሃያ አምስት በመቶ (25%) ደግሞ ቢያንስ ሁለተኛ ደረጃ ያጠናቀቁ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆን ስላለባቸው ይሄንኑ የሚያሟሉ እና

14. ሌሎች በመመሪያዎቹ የተገለፁ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

## ማሳሰቢያ፡-

1. በተባዕታይ ፆታ የተገለፀው ለአነስታይ ፆታም ይውላል፡፡
2. ጥቆማውን በዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ጋራድ ህንፃ 5ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ወይም በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 12752 አ.አ "ለዳሽን ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት" በመላክ ማቅረብ ይቻላል፡፡
3. የጥቆማ ማቅረቢያ ፎርሙ ከባንኩ ዋና መ/ቤት የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት ወይም ከባንኩ ከሁሉም ቅርንጫፎች ማግኘት ይቻላል፡፡
4. ለጥያቄና ማብራሪያ በአካል ዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ቦርድ ጽ/ቤት ደብረዘይት መንገድ ጋራድ ህንፃ አምስተኛ ፎቅ በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር **011-4-66-13-80 (Ext.232)** ወይም **011-1-58-61-86** ወይም **011-8-12-30-05/06** ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡
5. ከሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በኋላ የሚቀርቡ ጥቆማዎችም ሆኑ ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚደርሱ ጥቆማዎች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ

ዳሽን ባንክ አ.ማ

# ዳሽን ባንክ አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት መጠቆሚያ ቅፅ

# ተፅእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ብቻ የሚሞላ

# 1/3ተኛ ተጠቋሚዎችን በተመለከተ

1. የሚጠቆመው ግለሰብ /ድርጅት/ ስም (ግለሰብ ከሆነ ሙሉ ስም እስከነ አያት)
   1. ______________________________
   2. ______________________________
   3. ______________________________
   4. ______________________________
   5. ______________________________
   6. ______________________________
   7. ______________________________

2. የጠቋሚው ሙሉ ስም ____________________

   ፊርማ ____________________

   ቀን ______________ 2009 ዓ.ም

   የድርጅቱ ማህተም (ጠቋሚው ደርጅት ከሆነ)

3. ጠቋሚው የያዘው የአክስዮን መጠን

   ______________________

## ማሳሰቢያ፡-

1. ተፅእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክስዮኖች ማለት ከ 2% በታች የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክስዮኖች ማለት ነው፡፡
2. ጥቆማው በውክልና የቀረበ ከሆነ ውክልናው ጥቆማውን ማቅረብ የሚያስችል ሆኖ ፎቶ ኮፒው ከጥቆማ ማቅረቢያ ቅፁ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ከሚያዝያ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነው ጥቆማ ማቅረብ የሚቻለው፡፡ እስከ 7 ተጠቋሚዎች ድረስ መጠቆም ይቻላል፡፡
4. ጥቆማውን በዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ጋራድ ህንፃ 5ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት ወይም በባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ወይም በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 12752 አ.አ “ለዳሽን ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት” በመላክ ማቅረብ ይቻላል፡፡
5. የጥቆማ መስጫ ወረቀቱ በፖስታ ታሽጎ ሊመለስ የሚገባ ሲሆን ከሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. በኋላ ጥቆማ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄም ሆነ ከዚህ ጊዜ በኋላ ባንኩ ጋር የሚደርስ የጥቆማ መስጫ ወረቀት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በአክብሮት ይገልፃል፡፡

አስመራጭ ኮሚቴ

# ዳሽን ባንክ አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላት መጠቆሚያ ቅፅ

# በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚሞላ

# 2/3ተኛ ተጠቋሚዎችን በተመለከተ

1. የሚጠቆመው ግለሰብ /ድርጅት/ ስም (ግለሰብ ከሆነ ሙሉ ስም እስከነ አያት)
    1. ______________________________
    2. ______________________________
    3. ______________________________
    4. ______________________________
    5. ______________________________
    6. ______________________________
    7. ______________________________
    8. ______________________________
    9. ______________________________
    10. ______________________________
    11. ______________________________
    12. ______________________________
    13. ______________________________
    14. ______________________________

2. የጠቋሚው ሙሉ ስም ______________________

   ፊርማ ______________________

   ቀን ______________ 2009 ዓ.ም

   የድርጅቱ ማህተም (ጠቋሚው ደርጅት ከሆነ)

3. ጠቋሚው የያዘው የአክስዮን መጠን

   ______________________

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ጥቆማው በውክልና የቀረበ ከሆነ ውክልናው ጥቆማውን ማቅረብ የሚያስችል ሆኖ ፎቶ ኮፒው ከጥቆማ ማቅረቢያ ቅፁ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
2. ከሚያዝያ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነው ጥቆማ ማቅረብ የሚቻለው፡፡ እስከ 14 ተጠቋሚዎች ድረስ መጠቆም ይቻላል፡፡
3. ጥቆማውን በዳሽን ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ጋራድ ህንፃ 5ኛ ፎቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት ወይም በባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ወይም በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 12752 አ.አ "ለዳሽን ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጽ/ቤት" በመላክ ማቅረብ ይቻላል፡፡
4. የጥቆማ መስጫ ወረቀቱ በፖስታ ታሽጎ ሊመለስ የሚገባ ሲሆን ከሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. በኋላ ጥቆማ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄም ሆነ ከዚህ ጊዜ በኋላ ባንኩ ጋር የሚደርስ የጥቆማ መስጫ ወረቀት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በአክብሮት ይገልፃል፡፡

<u>አስመራጭ ኮሚቴ</u>